# ነፋስ ሰውን ነዳው!



ክርስቶስ ሲሰቀል ጎልጎታ ተራራ፣
መንጋው እልል ሲል በሳቅ በደስታ፣
ሶስት ብቻ ቀረ በእምነቱ የጠና፡፡

ዛሬ ፍትህ ስትሞት በምስማር ተወግታ፣
ከጎኗ የሚቆም ሶስትም ሰው ታጣ፡፡

እስተ ቀራኒዮ ብሎ ማዩ ሁሉ፣
ሲሶ መንገድ ሳይደርስ ተሰበረ ቃሉ፡፡

ፍትህ ስትሰቀል እልልታን ታሰማን፣
አኬልዳማን እንጅ ምኑን አለምአየን፡፡

የተገናኘ ስቃይ ከእንቅልፍ ሳያነቃው፣
የገናገፉ ስብከት እንደ ከበት ነዳው፡፡

ገዳዩ ጨፍጫፊው ደም አፍሳሹ ብሎ፣
ሩብ ክፍለ ዘመን ሲጮህበት ኖሮ፣
አቀፈና ሳመው ዛሬ አብዬ ብሎ!

የሰው የበግ መንጋን ምንድን ይለያቸው፣
አሳራጅ እረኛ እኩል ተነዳቸው?

ይብላኝ ለሞተ እንጅ ቋሚንስ ደልቶታል፣
ገዳዩ ሊሞሽር እስክስታ ያወርዳል፡፡

ላባ የሚከብደው የነፋስ ሸውታ፣
ምን ያህል ቢቀለው የሰውነት ገላ፣
አንስቶ አንሳፈፈው እንደ በጋ ትቢያ!

ጣምራ እጅ አያነሳው ሲባል የነበረው፣
የፓስተሩ ትንፋሽ ሲጠርገው አየነው፡፡

እየቀላቀለ ነፋስ ስልነዳው፣
ከባድና ቀላል እኩል ሆነ ዋጋው፡፡

የዚህ ዘመን ነፋስ ከዛር የከፋ ነው፣
እንኳን ገለባውን አለቱን አነሳው፡፡

ታጋዩ ጎመራ ደረጀ ስንለው፣
ትል የወጋው ዱባ ክፍት ሆኖ አገኘነው፡፡

በአልፎ ሃጂ ነፋስ የተወሰደ ሰው፣
ሰማዩ ሲሰክን ስካሩ ሲለቀው፣
በየ ቁጥቋጦው ሥር ወድቆ እሚገኝ ነው፣
ብርሃን ሲነጋ ወጥቶ መመልከት ነው፡፡

እባክህ ነፋሱ እረፍ አደብ ግዛ፣
በሰማዕት መቃብር አረምን አትዝራ!

እባክህ መለኮት ለሰው ክብደት ስጠው፣
እንደ ገብስ ገለባ ነፋሱ ጠረገው፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ህዳር 30 2012 ዓ.ም.